# የለውጥ መርህ - በአእምሮ መታደስ
## ክፍል ሶስት

### የተዋጀ /በመታደስ መለወጥን እያገኘ ያለ/ አእምሮ ገጽታዎች

1. *የእ/ርን ፈቃድ ያለችግር ያውቃል*

*የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍጹምም የሆነው ነገር ምን እንደ ሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ /mind/ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ። / ሮሜ 12፡2*

*ስለዚሁ እኛ ደግሞ ይህን ከሰማንበት ቀን ጀምረን የፈቃዱ እውቀት መንፈሳዊ ጥበብንና አእምሮን ሁሉ እንዲሞላባችሁ እየለመንን፥ ስለ እናንተ ጸሎትን አልተውንም። / ቆላስይስ 1፡9*

2. *የቃሉን አሳብ / መንፈስ ይረዳል*

*በዚያን ጊዜም መጻሕፍትን ያስተውሉ ዘንድ አእምሮአቸውን ከፈተላቸው / ሉቃ 24፡45*

3. *ለእ/ር ሕግ ይገዛል*

*የሰውንም አሳብ በእግዚአብሔርም እውቀት ላይ የሚነሣውን ከፍ ያለውን ነገር ሁሉ እናፈርሳለን ለክርስቶስም ለመታዘዝ አእምሮን ሁሉ እንማርካለን፥ / 2ኛ ቆሮ 10፡5*

*..እንግዲያስ እኔ በአእምሮዬ ለእግዚአብሔር ሕግ፥ በሥጋዬ ግን ለኃጢአት ሕግ እገዛለሁ። / ሮሜ 7፡25*

### የአእምሮ መታደስ እንዴት ይሆናል?

**1. ወደ ውስጣችን የምናስገባውን መምረጥ / የሚያዋጣንን ማወቅ**

*አላቸውም። ምን እንድትሰሙ ተጠበቁ። በምትሰፍሩበት መስፈሪያ ይሰፈርላችኋል ለእናንተም ይጨመርላችኋል። / ማር 4፡24*

*የሰው ሆድ ከአፉ ፍሬ ይሞላል ከንፈሩም ከሚያፈራው ይጠግባል። / ምሳ 18፡20*

**የማየት ሃይል**

- እ/ር ለአብርሃም የምድርን አሸዋ፣ የሰማይንም ከዋክብት ማሳየት ለምን አስፈለገው?
- ደግሞስ እ/ር ለኢሳይያስ ዙፋኑን፣ ለኤርሚያስ የለውዝ በትርን፣ ለሕዝቅኤል ወንዝን፣ ለአሞጽ ቱምቢን ያሳየበትን ምክንያት አስበህ ታውቃለህ?
- ኤልሳስ የኤልያስን መነጠቅ ማየት ለምን አስፈለገው? 2ኛ ነገ 2፡10
- ያዕቆብ በጎቹ በሚያዩት በትር አምሳል እንዲወልዱ ያደረገበት ሚስጥር ምንድን ነው? *ዘፍ 30፡37-43 "ያዕቆብም ልብን ለውዝ ኤርሞን ከሚባሉ እንጨቶች እርጥብ በትርን ወስዶ በበትሮቹ ውስጥ ያለው ነጭ እንዲታይ ነጭ ሽመልመሌ አድርጎ ላጣቸው። የላጣቸውንም በትሮች በጎቹ ውኃ ሊጠጡ በመጡ ጊዜ በውኃ ማጠጫው ገንዳ ውስጥ በበጎቹ ፊት አኖራቸው፤ በጎቹ ውኃ ሊጠጡ በመጡ ጊዜ ይጎመጁ ነበር። በጎቹም በትሮቹን አይተው ከመጎምጀታቸው የተነሣ ፀነሱ፤ በጎቹም ሽመልመሌ መሳይና ዝንጕርጕር ነቍጣም ያለበቱን ወለዱ። ...እንዲህም ሆነ፤ የበረቱት በጎች በጎመጁ ጊዜ ፥ በጎቹ በትሮቹን አይተው በበትሮቹ አምሳል ይፀንሱ ዘንድ ያዕቆብ በትሮቹን በውኃ ማጠጫው ገንዳ ውስጥ ከበጎቹ ፊት አደረገ.."*

በእርግጥም እ/ር በማየት ውስጥ ያስቀመጠው ልዩ ሃይል አለ። ከምንማረው ሰማንያ በመቶ በአእምሮአችን ላይ የሚቀረጸው በማየት የምንማረው እንደሆነ የስነ-አእምሮ አዋቂዎች ይናገራሉ። በአገራችንም በተለምዶ "በአይን የገባ ነገር በቀላሉ አይወጣም" የሚሉት አባባል ከዚህ ጋር የሚስማማ ነው። እንግዲህ የምናየውን ነገር የመምረጥ ሃላፊነት አለብን።

**2. አእምሮን በሰማያዊ ስፍራ መጥመድ / መንፈሳዊ አእምሮን ማዳበር**

*እንግዲህ ከክርስቶስ ጋር ከተነሣችሁ፥ ክርስቶስ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦ ባለበት በላይ ያለውን እሹ። በላይ ያለውን አስቡ እንጂ በምድር ያለውን አይደለም። /ቆላ 3፡1-2*

*ስለ ሥጋ ማሰብ (to be carnally minded) ሞት ነውና፥ ስለ መንፈስ ማሰብ (to be spiritually minded) ግን ሕይወትና ሰላም ነው። ስለ ሥጋ ማሰብ በእግዚአብሔር ዘንድ ጥል ነውና ለእግዚአብሔር ሕግ አይገዛምና፥ መገዛትም ተስኖታል። / ሮሜ 8፡6-7*

*ስለዚሁ እኛ ደግሞ ይህን ከሰማንበት ቀን ጀምረን የፈቃዱ እውቀት መንፈሳዊ ጥበብንና አእምሮን ሁሉ እንዲሞላባችሁ እየለመንን፥ ስለ እናንተ ጸሎትን አልተውንም። / ቆላ 1፡9*

**3. ማስለመድ / ተግሳጽ** (Discipline)

*ተግሣጽን ቸል የሚል የራሱን ነፍስ ይንቃል ዘለፋን የሚሰማ ግን አእምሮ ያገኛል። /ምሳሌ 15፡32*

*ሰውነትን ለሥጋዊ ነገር ማስለመድ ለጥቂት ይጠቅማልና እግዚአብሔርን መምሰል ግን የአሁንና የሚመጣው ሕይወት ተስፋ ስላለው፥ ለነገር ሁሉ ይጠቅማል። / 1ኛጢሞ 4፡8*

*ጠንካራ ምግብ ግን መልካሙንና ክፉውን ለመለየት በሥራቸው የለመደ ልቡና ላላቸው ለፍጹማን ሰዎች ነው። / ዕብ 5፡14*

*የእግዚአብሔር ቃል በሙላት ይኑርባችሁ። በጥበብ ሁሉ እርስ በርሳችሁ አስተምሩና ገሥጹ። በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ በጸጋው በልባችሁ ለእግዚአብሔር ዘምሩ። / ቆላ 3፡16*

## ምን ታዘናል?

*በፍጹም ልብ በፍጹም አእምሮም /ሃሳብ/ በፍጹም ነፍስም በፍጹም ኃይልም እርሱን መውደድ፥ ባልንጀራንም እንደ ራስ መውደድ በሙሉ ከሚቃጠል መሥዋዕትና ከሌላው መሥዋዕት ሁሉ የሚበልጥ ነው አለው። / ማር 12፡33*

*ወንድሞች ሆይ፥ በአእምሮ ሕፃናት አትሁኑ ለክፋት ነገር ሕፃናት ሁኑ እንጂ በአእምሮ የበሰሉ ሁኑ። / 1ኛ ቆሮ 14፡20*

*የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍጹምም የሆነው ነገር ምን እንደ ሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ /mind/ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ። / ሮሜ 12፡2*

*በአእምሮአችሁም መንፈስ ታደሱ፥ / ኤፌ 4፡23*

*እንግዲህ አሕዛብ ደግሞ በአእምሮአቸው ከንቱነት እንደሚመላለሱ ከእንግዲህ ወዲህ እንዳትመላለሱ እላለሁ በጌታም ሆኜ እመሰክራለሁ.. / ኤፌ 4፡17-24*

*እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ የእምነትን መጠን እንዳካፈለው፥ እንደ ባለ አእምሮ እንዲያስብ እንጂ ማሰብ ከሚገባው አልፎ በትዕቢት እንዳያስብ በመካከላችሁ ላለው ለእያንዳንዱ በተሰጠኝ ጸጋ እናገራለሁ። / ሮሜ 12፡3*

*ዳሩ ግን የነገር ሁሉ መጨረሻ ቀርቦአል። እንግዲህ <u>እንደ ባለ አእምሮ አስቡ</u>፥ / 1ኛ የጴጥ 4:7*

*እንግዲህ ከክርስቶስ ጋር ከተነሣችሁ፥ ክርስቶስ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦ ባለበት በላይ ያለውን እሹ።
<u>በላይ ያለውን አስቡ</u> እንጂ በምድር ያለውን አይደለም። / ቆላ 3:1-2*

## የተለመዱ የተሳሳቱ የአመለካከት ዘይቤዎችና መፍተሄዎቻቸው፡

1. **የተሸናፊነት ስሜት፡**
“ሃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ” ፊልጵ 4:13

2. **“የተሳሳተ አላማ ነው ያለህ፤ ራስህን ስለምትወድ ነው…” የሚል አሳብ**
የእ/ር አላማ በአንተ ላይ ነው!

3. **“አይገባህም” የሚል ስሜት**
የተገባህ መሆን አያስፈልግህም!

4. **ላንተ እንኳን ሊሆን አይችልም፤ ሁሉም እኮ አይሳካለትም**
“ለሚያምን ሁሉ ይቻላል” ተብሎ ተጽፎአል!

5. **ጊዜህ አልፎአል፤ ምንም ልታደርግ አትችልም**
ለአብርሃምና ለሳራም አላለፈባቸውም! ለጋለሞታይቱም ረአብ

*ጸጋውንም በጥበብና በአእምሮ ሁሉ አበዛልን። / ኤፌ 1:8*